**የዐለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አስፈጻሚ ቦርድ ለኢትዮጵያ የተዘጋጀውን የተራዘመ የብድር አገልግሎት ሁለተኛ ዙር ግምገማ አጠናቀቀ።**

- የዐለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አስፈጻሚ ቦርድ ለኢትዮጵያ የተዘጋጀውን የተራዘመ የብድር አገልግሎት ሁለተኛ ዙር ግምገማ አጠናቅቆ መንግሥት 248 ሚልሊዮን ዶላር (SDR 191.7 ሚሊዮን) እንዲወስድ ፈቅዷል። የተራዘመ የብድር አገልግሎቱ በሐምሌ 2015 ዓም በዐለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አስፈጻሚ ቦርድ የጸደቀው የልማት አጋሮች እና አበዳሪዎች ለኢትዮጵያ የሰጡት የ10.7 ቢሊዮን ዶላር የእርዳታ ጥቅል አካል ነው።
- የኢትዮጵያ መንግሥት የገንዘብ ድርጅቱ የሚያግዘውን ፕሮግራም አላማዎች በማሳካት ረገድ ጠንካራ ቁርጠኝነት አሳይቷል። የተራዘመ የብድር አገልግሎቱ የሚያግዛቸው ማሻሻያዎች አተገባበርም በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ ነው።

**ዋሺንግተን ዲሲ፡** የዐለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አስፈጻሚ ቦርድ በዛሬው ዕለት ለኢትዮጵያ የተዘጋጀውን እና 48 ወራት የሚፈጀውን የተራዘመ የብድር አገልግሎት ሁለተኛ ዙር ግምገማ አጠናቋል። የቦርዱ ውሳኔ ኢትዮጵያ የባልንስ ኦፍ ፔይመንት ፍላጎቷን ለማሟላት የሚያግዛትን 248 ሚልሊዮን ዶላር (SDR 191.7 ሚሊዮን) በአስቸኳይ እንዲተላለፍላት የሚያስችል ነው። የአሁኑ ግምገማ መጠናቀቅ በዚህ ሂደት ውስጥ እስካሁን የተላለፈውን አጠቃላይ የገንዘብ መጠን ወደ 1.611 ቢሊዮን ዶላር ያስጠጋዋል።

ለኢትዮጵያ የተዘጋጀው የSDR 2.556 ቢሊዮን (የኮታው 850 ፐርሰንት) መጠን ወይም ፕሮግራሙ በሐምሌ 22 ቀን 2015 ዓም በጸደቀበት ጊዜ 3.4 ቢሊዮን ዶላር የነበረው የገንዘብ መጠን የማክሮ ኢኮኖሚ አለመጣጣሞችን ለመፍታት እና በግሉ ዘርፍ ለሚመራ እድገት መሠረት ለመጣል በመንግሥት የተቀረጸውን የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳ የመደገፍ አላማ ያለው ነው።

ሁሉም ኳሊቴቲቭ የአፈጻጸም መስፈርቶች ተሟልተዋል። መንግሥት ኢላማ ለተደረጉ የማህበራዊ ሴፍቲ ኔት ሥራዎች ያደረገው አስተዋጽኦ ከታለመው ያነሰ ሲሆን፤ ይህም በአመዛኙ የሴፍቲ ኔት ፕሮግራሞችን ለማስፋፋት እንዲሁም በከፍተኛ ደረጃ የጨመረውን የበጀት ፍላጎት ለማሟላት ዝግጅት ያስፈልግ ስለነበረ ነው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ኦዲት የተደረጉ ሒሳቦች ማጠናቀቂያ መዋቅራዊ/ተቋማዊ መነሻ ሥራውን ማጠናቀቂያ ጊዜ ለመስጠት ሲባል ከጥር ወር 2017 ዓም እስከ መጋቢት ወር 2017 ዓም ሆኖ እንዲስተካከል ተደርጓል።

የገበያውን ውጤጣማነት ለማጠናከር መንግሥት መጠነ ሰፊ የፖሊሲ እርምጃዎች በመውሰዱ የውጪ ምንዛሬ ገበያ አሠራር መሻሻል እያሳየ ቀጥሏል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ጠበቅ ያሉ ሞኒታሪ እና ገንዘብ ነክ ሁኔታዎችን ተግባራዊ ከማድረጉም በላይ የሞኒታሪ ፖሊሲ ማዕቀፉን የማዘመኑ ሥራም እየገሠገሠ ነው። እስካሁን የተገኙትን ስኬቶች ለማስቀጠል አሁንም ያልተቋረጠ ቁርጠኝነት የሚያስፈልግ ቢሆንም የተከናወነው የሀገር ውስጥ የፊስካል ገቢዎችን የመሰብሰብ፣ በመንግሥት ባለቤትነት ስር የሚገኙ የንግድ ድርጅቶችን የማጠናከር እንዲሁም ገንዘብ ነክ መረጋጋትን የማቆየት ሥራ ተስፋ የሚጣልበት ነው። ማህበራዊ ሴፍቲ ኔቶችን ማስፋፋት ማሻሻያዎቹ በተጋላጭ ኅብረተሰብ ላይ የሚያስከትሉትን ተጽእኖ በመቀነስ ረገድ ወሳኝ ጉዳይ ነው።

መንግሥትም የdebt sustainabilityን ለማስመለስ ጥረቱን ከመቀጠሉም በላይ የdebt treatmentን ለማስከበርም እርምጃዎችን እየወሰደ ይገኛል። በጋራ ማዕቀፉ ስር የተካሄደው የdebt restructuring ድርድር ግሥጋሤም በበጎ ዐይን የሚታይ ነው። የተገኙት ገንዘብ ነክ ማረጋገጫዎች እና የተድረጉ የማስተካከያ ጥረቶችም ከዐለም ቀፍ የገንዘብ ድርጅት የፖሊሲ እና የፕሮግራም መስፈርቶች ጋር የተጣጣሙ ናቸው።

የአስፈጻሚ ቦርዱን ውሳኔ ተከትሎ ምክትል ማኔጂንግ ዳይሬክተር እና የቦርዱ ሰብሳቢ አቶ ናይጅል ክላርክ የሚከተለውን መልዕክት አስተላልፈዋል።

“መንግሥት በድርጅቱ የሚደገፈውን ፕሮግራም በመተግበር እንዲሁም የማክሮ ኢኮኖሚ አለመጣጣሞችን በመፍታት ረገድ ጠንካራ እንቅስቃሴ ማድረጉን ቀጥሏል። ወደ ተለዋዋጭ የውጪ ምንዛሬ መጠን የተደረገው ሽግግር

በማክሮ ኢኮኖሚ እና በውጪ ምንዛሬ ገበያ ፖሊሲ እርምጃዎች ተደግፎ ወደ ፊት እየገፋ ሲሆን፤ የትይዩ ገበያ ፕሪሚየምም እየጨመረ ከመጣው የምንዛሬ አቅርቦት አንጻር በነጠላ ዲጂት ደረጃ መረጋጋት አሳይቷል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን የውጪ ምንዛሬ እንቅስቃሴዎች እንዲሁም የውጪ ምንዛሬ ገበያ ልማትን የሚደግፉ ተጨማሪ የፖሊሲ እርምጃዎችን ማስቀጠል የገበያውን ውጤታማነት እና ጥልቅነት ከማስቀጠል አንጻር ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው። ቀጣይነት ያለው ጥብቅ የሞኒታሪ ፖሊሲን ማስቀጠልን እና የመንግሥትን የገንዘብ ጉድለቶች በሞኒታሪ ፋይናንሲንግ የመደግፍን አሠራር ማስቀረትን የመሳሰሉ ብልህነት የተሞሉ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎች አለምጣጣሞችን ለመቀነስ እንዲሁም የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋትን ለማምጣት መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው።

አዎንታዊ እና እውነተኛ የሞኒታሪ የፖሊሲ መጠን ላይ መድረስ የአዲሱን የሞኒታሪ ፖሊሲ ማዕቀፍ አስተማማኝነት/ተአማኒነት ለማሳደግ እንዲሁም ከዋጋ ግሽበት እና ከውጪ ምንዝሬ አንጻር ከገበያው የሚጠበቀውን ነገር ለመለወጥ ቁልፍ የሆነ እርምጃ ነው። በተጨማሪም መንግሥት የክሬዲት እድገት ጣሪያን እና የፖሊሲ መጠን ለውጦችን የማስቀረትን ሥራ በጥንቃቄ አከታትሎ መሥራት እንዲሁም ከፖሊሲ ጀርባ የሚገኙ ሐሳቦችን በግልጽ ማሳወቅ አለበት። ለባንኮች የተቀመጡ net open position ደንቦችን በቅርበት መከታተል እና ማስፈጸም የገንዘብ ዘርፉን ተጋላጭነቶች በመፍታት ረገድ ያግዛል።

በ2017 ዓም ኅዳር ወር መጨረሻ አካባቢ በፓርላማ የጸደቀው ተጨማሪ በጀት የፊስካል ኢላማዎች ከፕሮግራም አላማዎች ጋር ተናባቢ ሆነው እንዲቆዩ የሚያደርግ ነው። መንግሥትም ተጋላጭ ቤተሰቦችን ለመታደግ እንዲሁም የመንግሥት ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ የታለመውን የማህበራዊ ሴፍቲ ኔት (PSNP) የማስፋፋት ጥረትን ማፋጠን አለበት። በነዳጅ ዋጋ አማካኝነት ወጪውን ሙሉ በሙሉ ማስመለስ ተጨማሪ ገቢን ለማሰባሰብ እንዲሁም የፊስካል ቋትን መልሶ ለመገንባት/ለመሙላት በጣም አስፈላጊ ነው። የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የኤክሳይስ ታክስ አፈጻጸምን የመሳሰሉ ዘላቂነት ያላቸው የግብር ገቢ ማሰባሰቢያ ጥረቶች ለማህበራዊ እና ለልማት ሥራዎች ለሚያስፈልግ ወጪ በቂ አቅም ለመፍጠር ሲባል የሚቀጥሉ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን አስተዳደር በተመለከተ የወጣው አዲስ ሕግ በተለያየ መልኩ በነባሩ የሕግ ማዕቀፍ ላይ የተደረጉ ከፍተኛ ለውጦች ማሳያ ነው። ይሁን እንጂ ከአስተዳደር እና ከነጻነት አንጻር አሁንም የቀሩ ክፍተቶችን መሙላት ያስፈልጋል።

የባንክ አስተዳደር የሕግ ማዕቀፍን ማዘመንን፣ የባንክ ክትትልን ማጠናከርን እንዲሁም የማይፈጸሙ/የተበላሹ ብድሮችን መከታተልን የመሳሰሉ የገንዘብ ዘርፍ ማሻሻያዎችን እየተገበሩ መቀጠል ለገንዘብ ዘርፉ መረጋጋት እገዛ ያደርጋል።

በG20 የጋራ ማዕቀፍ ስር ከሚገኘው Official Credit Committee ጋር debt treatmentን በተመለከተ እስካሁን የተደረገው ከፍተኛ እንቅስቃሴ የdebt sustainabilityን ከማስመለስ አንጻር በጣም ጠቃሚ እርምጃ ነው። መንግሥት ሶስተኛው ዙር ግምገማ በሚደረግበት ጊዜ የመግባቢያ ስምምነት ላይ ለመድረስ እየሠራ ከመሆኑም በተጨማሪ ጎን ለጎን ደግሞ ከዩሮ ቦንድ ባለቤቶች እና ሌሎች ውጫዊ የንግድ አበዳሪዎች ጋር ተነጻጻሪ አግባብ ላይ ለመድረስም እንቅስቃሴ እያደረገ ነው።”

**የተመረጡ የኢኮኖሚ አመልካቾች ለኢትዮጵያ፤ 2013/14 እስከ 2020/21**

| | 2013/14 | 2014/15 | 2015/16 | 2016/17 | 2017/18 | 2018/19 | 2019/20 | 2020/21 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | Prel | Proj | Proj | Proj | Proj | Proj |
| **ውጤት** | | | | | | | | |
| እውነተኛ የጂዲፒፒ እድገት (%) | 6.4 | 7.2 | 8.1 | 6.6 | 7.1 | 7.7 | 8.0 | 7.8 |
| **ዋጋዎች** | | | | | | | | |
| የዋጋ ግሽበት (%) | 33.9 | 32.5 | 26.6 | 20.7 | 16.9 | 10.6 | 9.5 | 8.8 |
| **ጠቅላላ የመንግሥት ገንዘብ** | | | | | | | | |
| ገቢ (የጂዲፒ %) | 8.1 | 7.9 | 7.3 | 8.5 | 9.8 | 10.8 | 11.2 | 11.4 |
| ወጪ (የጂዲፒ %) | 12.7 | 10.8 | 9.5 | 11.6 | 12.3 | 13.2 | 13.4 | 13.4 |
| የፊስካል ባላንስ እርዳታን ጨምሮ (የጂዲፒ %) | -4.2 | -2.6 | -2.0 | -1.7 | -2.0 | -1.9 | -1.7 | -1.5 |
| የመንግሥት እዳ (የጂዲፒ %)[1] | 48.9 | 40.2 | 34.4 | 45.6 | 39.8 | 36.9 | 34.4 | 32.2 |
| **ገንዘብ እና ብድር** | | | | | | | | |
| አጠቃላይ ገንዘብ (% change) | 27.2 | 26.6 | 14.1 | 26.1 | 29.3 | 29.4 | 21.3 | 20.4 |
| ለግል ዘርፍ እና ለመንግሥት የንግድ ድርጅቶች የተሰጠ ብድር (% change)[2] | 18.9 | 24.1 | 9.7 | -24.0 | 42.2 | 42.6 | 25.6 | 23.2 |

[1] ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሚጠበቁ የረጅም ጊዜ የውጪ ሀገር ክፍያዎችን እና ኢትዮቴሌኮም ከውጪ የተበደራቸውን ብድሮች ጨምሮ የመግሥት እና መንግሥት ዋስትና የሰጠባቸው የውጪ እዳዎች። የሚጠበቁ የእዳ እፎይታዎችን አያካትትም።

[2] የ2017/18 ትንበያዎች የኢትዮፒያ ንግድ ባንክ ረካፒታላይዜሽን ተጽእኖን ያካትታሉ።

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ባላንስ ኦፍ ፔይመንትስ** | | | | | | | | |
| ወቅታዊ ሒሳብ (የጂዲፒ %) | -4.0 | -2.9 | -2.9 | -4.4 | -3.0 | -2.5 | -2.1 | -2.0 |
| ቀጥተኛ የውጪ ኢንቨስትመንት (የጂዲፒ %) | 2.6 | 2.1 | 1.9 | 3.4 | 3.2 | 2.9 | 3.0 | 3.0 |
| ገቢ (በገቢ ንግድ ወራት ውስጥ) | 0.8 | 0.5 | 0.7 | 1.4 | 2.1 | 2.6 | 3.5 | 3.5 |
| የውጪ እዳ (የጂዲፒ %) | 24.0 | 18.1 | 15.1 | 29.3 | 26.2 | 24.0 | 21.9 | 19.1 |
| **የምንዛሬ መጠን** | | | | | | | | |
| እውነተኛ ውጤታማ የምንዛሬ መጠን (ለውጥ፣ የጊዜ መጨረሻ ዲፕሪሺዬሽን %) | 10.3 | 27.9 | 12.6 | … | … | … | … | … |